# ፊት ነሷቸው

ታዛቢው

ወላጅማ ወላጅ ፡ እናት ነሽ ለሰው
አለመታደልሽ ፡ የእድልሽ መጥመሙ
ልጅ አለኝ አትበይ ፡ ከንቱ ነው ድካሙ
ተካፍለው ካይበሉ ፡ ጡትሽን ሲቃሙ
እንግልት ስቃዩ ፡ በዝቶብሽ ህመሙ
መድሃኒቱን አጥቶ ፡ ምሁሩ ሐኪሙ
ሞተሽ ልታርፊው ነው ፡ እስከ ዘላለሙ ፡፡

አንዳርጋቸው ብሎ ፡ ጸሎት ዳቢሎስጋ
አማላጅ የሚሆን ፡ ብርቱ ካህን ፍለጋ
ጨላማ እየዋጠን ፡ ካልን ብርሃን ነጋ
አገር በነገደ ፡ ዙፋን ሲረጋጋ
ቀድሞ የማናውቀው ፡ ቅቤ አለት ከወጋ
ምድር ቀውጢ ሆነች ፡ ወያኔ ተናጋ፡፡

የተገላቢጦሽ ፡ ወሬ እያቀጠነ
ዳር ዳሩን ፡ ይጮሀል ፡ እየተጀነነ
ልኩን ስለማያውቅ ፡ መስሎት የገነነ
ዕብጠትም፡ ወርድ አለው ፡ እየተመጠነ
አንበሳ ቢያሸልብ ፡ ጥንቸል ሰለጠነ
ምን ሃጢያት ይፈራል ፡ እንደ የተኮነነ ፡፡

የሰው ነብስ የበሉ ፡ ደም ያሰከራቸው
የደርግ ባለሚል ፡ ነግሰው ያየናቸው
ከወያኔ ያደሩ ፡ ወኔ የሌላቸው
የሚወላውሉ ፡ ቆሌ የራቃቸው
በየድርጅቱ ፡ መበተን ሙያቸው
ያከፈው ሥራቸው ፡ መች ተረሳላቸው
የትግል ደንቃሮች ፡ ምንድነው ጥሪያቸው
ፊት ነሷቸው እንጂ ፡ ማን ፊት አመጣቸው ፡፡